# *በአርቲስት ቴድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ላይ ብይን ተሰጠ፡፡ አርቲስቱን ደግፈው ይፈታ ያሉ ታሰሩ፡ የቀድሞ የቅንጅት አመራር አባላት ይገኙበታል፡፡*

በሰኔ 27 2000 ዓ.ም የዋለው ችሎት በክሱ ላይ ብይን ለመስጠት ለዛሬ ሐምሌ 14 2000 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቶ የነበረ ሲሆን በዛሬው እለት ባዋለው ችሎት ተከሳሽ ቴድሮስ ካሳሁን ላይ የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ የሚቃረን ሆኖ ስላላገኘው ክሱን እንዲከላከል ሲል ወስኖበታል፡፡

አርቲስት ቴድሮስ ካሳሁን ባለፈው ዓመት ጥቅምት 23 ከለሊቱ 7፡10 ገደማ የግል ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2 59869 ኢ.አ በሆነ ቢ.ኤ.ም ደብሊው መኪና ደጉ ይበልጣል የተባለ ግለሰብን ገጭቶ በማምለጥ ነው የተከሰሰው፡፡ ፖሊስ በጥቅምት 24 1999ዓ.ም አርቲስቱን ከመኖሪያ ቤቱ በመያዝ ሰው ገጭተህ አምልጠሀል ብሎ ከሶት የነበረ ሲሆን በጊዜው የ50ሺህ ብር ዋስትና ጠርወቶ ተለቆ ነበር፡፡

ዓቃቤ ሕግ ክሱን የሚያጠናክርልኝ ማስረጃ አግኝቻለሁ በማለት ክሱን የቀሰቀሰ ሲሆን አርቲስት ቴድሮስም ከአራት ወራት በፊት ጀምሮ የዋስትና መብቱን ተነፍጎ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ክሱን ሲከታተል ቆይታል፡፡ ቴዲ አፍሮ የተከሰሰበት ወንጀል በቸልተኝነት ሰው ገጭቶ በማምለጥ፣ ጠጥቶ በማሽከርከርና ያለመንጃ ፍቃድ መንዳት በሚል በ1996 የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543/3፣ የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 279/1956 አንቀፅ 5/4 እንዲሁም በ1996 የወጣውን የወንጀል ህግ 575/2 የተመለከተውን ሕግ መተላለፍ በሚል በመዝገብ ቁጥር 62266 ነው የተከሰሰው፡፡

በዛሬው እለት በልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትህ አዳራሽ በዋለው ችሎት አርቲስቱ የዋስትና መብቱ ይጠበቅለታል፣ ከእስር ነፃይወጣል ተብሎ ተጠብቆ ነበር፡፡ነገርግን ዳኛው ልዑል ገብረማርያም የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ቃል እና ፖሊስ ያቀረበው ማስረጃ ግለሰቡ በፍጥነት ሲነዳና ሲገጭ መታየቱን የሚያረጋግጡ፣ እርስ በርሳቸው የማይጋጩ ሆነው አግኝተናቸዋል፣ ስለዚህ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የሚያስከለክል ስለሆነ በማረፊያ ቤት ሆኖ እንዲከላከል ወስነናል ሲሉ ብይናቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ዳኛው የተከሳሽ ጠበቃ መከላከያ ይኖረው እንደሆን ጠይቀው፡ የአርቲስቱ ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አሰፋ መከላከያቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ ለችሎቱ አስረደተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የ2000 ዓ.ም የፍርድ ቤት የስራ ዘመን መጠናቀቂያ በመሆኑ ተከሳሽና ጠበቃው መስከረም 29 2001 ዓ.ም የመከላከያ ማስረጃቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ትእዛዝ በማስተላለፍ ችሎቱን በትነዋል፡፡ ቴድሮስ ከችሎቱ ሲወጣ በከፍተኛ የመከፋት ስሜት ውስጥ ገብቶ የነበረ ሲሆን ከአድናቂዎቹ፣ ከቅርብ ጓደኞቹና ዘመዶቹ የማፅናኛ ቃላት ሲሰነዘሩለት ነበር፡፡ እርሱም ችሎቱን ለቆ ሲወጣ እግዚአብሄር ታላቅ ነው የሚል ቃሉን በከፍተኛ ድምፅ አሰምታል፡፡

ዳኛ ልዑል ገ/ማርያም የቀድሞ ቅንጅት አመሮችን ክስ በቀኝ ዳኝነት ያስፈፀሙ ሲሆን የቴድሮስ ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አሰፋ ደግሞ ለምርጫ ቦርድ ወግነው ቅንጅትን መሞገታቸው የሚታወስ ነው፡፡

በተያያዘ ዜና ዛሬ የዋለውን የአርቲስት ቴድሮስ ካሳሁንን የፈርድ ሂደት ለመከታተል ከተገኙ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ቴድሮስ ከችሎት ሲወጣ ተከትለው የወጡና በደጅ ሲጠባበቁ ከነበሩት መሀከል ይፈታ የሚሉና አፅናኝ ቃላትን ሲሰነዝሩ ከነበሩት መሀከል የተወሰኑ ግለሰቦች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው ወደ ወረዳ ሶስት ፖሊስ ጣቢያ ተወስደዋል፡፡

እስካሁን እርግጠኛ ቁጥራቸውን ለማወቅ ባይቻልም፣ ሴቶች በኩል አምስት ሰዎች መያዛቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከቅንጅት አመራሮች ጋር በተመሳሳይ የክስ መዝገብ ተከሳ 15 ዓመት የተፈረደባትና በይቅርታ የተለቀቀቸው ቅድስት በቀለ ትገኝበታለች፡፡